# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

## Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

efdpu@aol.com www. Finote.org

**ፕሮግራም**:- ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት እስከ ሶስት ሰዓት በ 13 ሜትር ባንድ

**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.

## ዜና ዘገባ

***ሚያዚያ 29 ቀን 2003 ዓ.ም***

**የዓለም የፕሬስ ቀን በሒልተን ሆቲል ሊከበር የነበረው በውዝግብ ተበተነ ፤**

**የወያኔ ካድሬዎችም ስብሰባ ረግጠው ወጡ፤**

**በመቀሌ ዜጎች በፌዴራል ፖሊስ ተቀጠቀጡ፤**

**ታቦት የተሸከሙ እምነት አባቶችም በፖሊስ ተደበደቡ፤**

የፕሬስ ነፃትን ደፍጥጦና ደምስሶ ከዓለም ጭራ ደረጃ ያለው የወያኔ ቡድን የዓለም የፕሬስ ቀን በሚከበርበት ዕለትም ሌላ አፈና መፈፀሙ ተጋለጠ። ማክሰኞ ሚያዚያ 25 ቀን 2003 ዓ.ም በሂልተን ሆቲል በውይይት ተከብሮ ሊውል በነበረው የዓመታዊ ፕሬስ ቀን ላይ የወያኔ ቡድን በሰራው ሸፍጥ የተነሳ የተጠሩ እንግዶች እና የግል ጋዜጣ አዘጋጆች ስብሰባውን ረግጠው መውጣታቸው ታውቆዋል።

ይሄው የዓለም አቀፍ ቀን ሲከበር በሀገር ውስጥ ባሉ የፕሬስ ችግሮች ዙሪያ ውይይት እንዲደረግበት በሚል አስቀድሞ በተያዘው ፕሮግራም መሰረት የመድረክ መሪዎች ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲና ከህግ ባለሙያዎች እንዲሁም ከግል ፕሬስ አዘጋጆች የተውጣጣ ቡድን ተመድቦ የነበረ ቢሆንም የስብሰባው ሁኔታ ያስደነገጠው የወያኔ ቡድን ግን በስብሰባው ዕለት ድንገት ሳይታሰብ በለመደው የቆረጣ ስልቱ ሌሎች የወያኔ ቀንደኛ አባሎችን መድረክ እንዲመሩ በመደረጉ በብጥጥብጥ ተጀምሮ ስብሰባ ረግጦ እስከ መበተን እንደደረሰ ለማወቅ ተችሎዋል።

የዓለም የፕሬስ ቀን ሲከበር በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የፕሬስ እንቅስቃሴና ሁኔታው ብሎም የ20 ዓመት ጉዞው በሚል በተቀረፀው ፕሮግራም መሰረት የግል ጋዜጣ አዘጋጆች ......ወያኔ ያቋዋቋዋማቸው ማህበራት አመራሮች..... ታዋቂ ምሁራኖች.... የህግ ባለሙያዎች እና ሌሎች ጥሪ የተደረገላቸው የወያኔ ቱባ ባለስልጣናት ጭምር የተገኙ ቢሆንም ስብሰባው ሊጀመር ጥቂት ደቂቃዎች ሲቀረው የመድረኩ መሪዎች መቀየራቸውን ያወቁት የግል ጋዜጣ አዘጋጆች በመበሳጨት እንዲህ ያለ ሸፍጥ

የሚሰራ ከሆነ ስብሰባውን ረግጠን እንወጣለን ስለዚህ ይህን እርምጃ ከመውሰዳችን በፊት አስቀድሞ በተበተነው ፕሮግራም መሰረት መድረክ መሪዎቹ ይቀየሩ ብለው ሀሳብ ቢያቀርቡም እብሪተኛው የወያኔ ተላላኪ የሆነው ሽመልስ ከማል የተባለው አፍለኛ ካድሬ እሺ ከማለት ይልቅ እምቢ በማለቱ ስብሰባውን ረግጠው የወጡ ሲሆን ከእነሱም ጋር አብረው የተጠሩት እንግዶችና ባለስልጣናቱ ጭምር አዳራሹን ጥለው እንደወጡ በቦታው ከነበሩ የዓይን እማኞች ገለፃ ለማወቅ ተችሎዋል፡፡

ዕለቱን የፕሬስ ቀን ይወሳበታል... ይዘከርበታል .....ለቀጣዩም ይወራበታል ተብሎ የነበረውን ፕሮግራም በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሳይንስ እና ባህል ድርጅት (ዩኔስኮ) ድጋፍ የተዘጋጀ ቢሆንም ገንዘቡን በመንግስት ኮሙኒኬሽን መስሪያ ቤት በኩል ገቢ አድርገው ከመውሰዳቸውም በተጨማሪ ለፕሮግራሙ መሪዎች የተመደበውን ገንዘብ ሽመልስ ከማል እና አለቃው በረከት ስምኦን በጋራ የት እንዳዳረሱት ሳይታወቅ ፕሮግራሙም የተያዘለት ዓላማ ግቡን ሳይመታ መቅረቱም ታውቆዋል፡፡

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት መልዕክተኛ በፕሮግራሙ ላይ በተጠቀሰው ሰዓት የተገኙ ቢሆንም እነ ሽመልስ ከማል ያዘጋጁት የቀረጣ ስልት እስኪመቻች ድረስ ከነበረበት አንድ ሰዓት በላይ ዘግይቶ የተጀመረው ፕሮግራመ የታሰበው ሳይሆን ቀርቶ ስብሰባው ያለ ውጤት ሊበተን ችሎዋል፡፡

አስቀድሞ የተበተነው ፕሮግራም ለተሰብሳቢዎቹና ለእንግዶቹ የደረሰ ቢሆንም በሁኔታው የተደናገጡት ሽመልስና ጭፍሮቹ ወዲያው አዲስ ፕሮግራም አጽፈው የበተኑ መሆኑ ተሰብሳቢውን ግራ ያገባ ከመሆኑም በሻገር ራሳቸው የወያኔ ካድሬዎች ጭምር በድርጊቱ ማዘናቸውን ሲናገሩ ተደምጠዋል፡፡

በየአመቱ ሜይ 3 ዓለም አቀፍ የፕሬስ ቀን በሚል ታስቦ እንዲውል የተባበሩት መንግስታት ድርጅት በወሰነው መሰረት ዘንድሮ ማክሰኞ 25 ቀን 2003 ዓ.ም በሒልተን ሆቴል ውስጥ ሊደረግ የነበረው ውይይት በእነ ሽመልስ ከማል በተወሰደው የቀረጣ እርምጃ ያለ ውጤት መበተኑ ወያኔ የፕሬስ አፋኝ ከተባሉት አምባገነን በላይ መሆኑን የእለቱ የክብር እንግዳ ጭምር ታዝበው እንዲሔዱ አድረጎዋቸዋል፡፡

በፕሬስ ነፃነት ላይ የሚፈፀም ጥቃት በዓለም ዓቀፍ ህግ ላይ የሚፈጸም ጥቃት እንደሆነ የመንግስታቱ ድርጅት ዋና ፀሐፊ ባንኪሙን የላኩትን መልዕክት ተወካያቸው በንባብ ባሰሙበት ዕለት እንዲህ ያለ አሳፋሪ ተግባር መፈጸሙ አሳፋሪና አሳዛኝ ታሪክ ነው ሲሉ ተሰብሳቢዎቹ በብስጭት ሲገልጹም ተደምጠዋል፡፡

በሒልተን ሆቴል ሊከበር በነበረው የፕሬስ ቀን በዓል ላይ ውዝግብ ተፈጥሮ ስብሰባው ያለ ውጤት ከመበተኑ ጥቂት ደቂቃ ቀደም ብሎ የመንግስታቱ ድርጅት ዋና ጸሐፊ መልዕክተኛ ባደረጉት ንግግር ላይ በፕሬስ ነፃነት ላይ የተቃጡ ጥቃቶች ....... የሰብአዊ መብቶች ላይ...... በነጻነት በራሱ ላይ...... በአጠቃላይ የተባበሩት መንግስታት በቆመላቸው ላይ ሁሉ የተቃጡ ጥቃቶች ናቸው ሲሉ የዋና ጸሐፊውን መልዕክት በይፋ ገልጸዋል፡፡

ወያኔ በፕሬሱ ላይ የፈጸመውን ወንጀልና አፈና ጠንቅቀው የሚያውቁት የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ጸሀፊ በላኩት መልዕክት ላይ በግልጽ ያስቀመጡ መሆኑ ያበሳጨው የወያኔ ተላላኪው ሽመልስ ከማል ቡድኑ ለ20 ዓመታት የፈጸመውን ወንጀል ለመሸፈን ሲል በሀገሪቱ

የግልና የመንግስት ፕሬስ መሀከል በተፈጠረ መፋጠጥ የተፈጠረ ችግር ነው ሲል ለማስተባበል ሞክሮዋል።

ይሄው ግለሰብ እንደተናገረው ከሆነ የግል ፕሬሱን በአብዛኛው ተቆጣጥረውት የነበረው የወደቀው የደርግ ስርዓት አቀንቃኞች እና አገልጋዮች በመሆናቸው የእሱን የፖለቲካ ርዕዮት የሚከተሉ ነበሩ ሲልም የራሱን ገመና ለመሸፈን ሲል እያጣጣለ ሲናገር ተደምጦዋል።

ከመክፈቻው ንግግር በሁዋላ የተከናወኑ ድርጊቶች ውይይት እንዲደረግባቸው አስቀድሞ የተያዙ ፕሮግራሞች ቢኖሩም በእነ ሽመልስ ከማል ቀርጦ ቀጥል ጭፍንተኝነት የተነሳ ሳይሳካ ቀርቶዋል። በተለይ መገናኛ ብዙሀን ከህዝብ ጥቅም አኩዋያ በሚል ርዕስ ቀርቦ የነበረው ውይይት ብዙ ሳይኬድበት ተድበስብሶ እንዲያልፍ በማድረጋቸው ተሰብሳቢዎቹ እያጨበጨቡ ተቃውሞ ሲያሰሙም ተደምጦዋል።

የሚቀጥለውን ፕሮግራም ለመጀመር በአዘጋጆቹና በተጋባዦቹ መሀከል የመድረክ መሪዎቹን በተመለከተ አለመግባባት የተፈጠረ ሲሆን ቀድሞ መድረክ የያዙትና ቦታውን በኃይል የተቆጣጠሩት የእነ ሽመልስ ከማል ጋሻ ጃግሬዎች ለዕለቱ ፕሮግራም መሪዎች መስጠትና ማስረከብ ሲገባቸው አሻፈረኝ በማለታቸው የተነሳ ውዝግብ መፈጠሩ ታውቆዋል።

መድረኩን መያዝ ከሚገባቸውና ተሰብሳቢውን ከሚያወያዩት መሀከል አንዱ የነበረው የአውራ አምባ ጋዜጣ ዋና ስራ አስኪያጅ ጋዜጠኛ ዳዊት ከበደ ቦታውን እንዳይዝና በምትኩ አስቀድሞ በፕሮግራሙ ላይ ያልተካተቱ ስማቸው በፍጹም ያልሰፈረ ከኮሙኒኬሽን ጽህፈት ቤት..... ከብሮድ ካስት ባለስልጣን .....ከሬዲዮ ፋና .....እውቀቱ በሌላቸው በወያኔ ካድሬዎች ተጠልፎ የታሰበለት ዓላማ ፈሩን ስቶ በመገኘቱ ተሰብሳቢዎቹ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት አዳራሹን ጥለው መውጣታቸው ታውቆዋል።

ጋዜጠኛ ዳዊት ከበደ በዕለቱ ከመበሳጨቱ የተነሳ የዓለም የፕሬስ ነጻነት ቀን ልናከብር የመጣነውን የፕሬስ ሰዎች የዓለም የፕሬስ ሳንሱር ቀን ሰለባ ሆነን ዝግጅቱን ጥለን ልንወጣ ተገድደናል ሲል አምርሮ ሲገልፅም ተደምጦዋል።

አስገራሚውና አስደናቂው ታሪክ የወያኔ የመገናኛ በዙሀን ሰራተኞች እና ለወያኔ ያደሩ ናቸው የተባሉ ግለሰቦች ጭምር በእነ ሽመልስ ከማል ድርጊት ተበሳጭተው ስብሰባ ረግጠው መውጣታቸውን የጠቆመው የደረሰን ዘገባ በተለይ በበቲሌቪዥን እና በራዲዮ ጋዜጠኝነት ስራ ላይ ያሉ ጋዜጠኞች አለቃቸው በወሰደው እርምጃ በመበሳጨት ጥለው መውጣታቸው እነሱም ለውጥ ፈላጊ ናቸውን? የሚል ጥያቄ አስነስቷል። ።

በኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ ዘርፍ ምሁራኖች ተሰባስበው ስራ ለመጀመር በተደጋጋሚ ግዜ ፍቃድ ቢጠይቁም የተከለከሉ ሲሆን ለራሱ ለወያኔ ድርጅት ግን ቁጥሩ የበዛ ጣቢያዎችን እየከፈተ በስራ ላይ ከማዋሉም በተጨማሪ ከራዲዮ እስከ ቲሌቪዥን....... ከአጭር ሞገድ እስከ ኤፍ ኤም ድረስ ተቆጣጥሮ ይገኛል።

በህዝቡ ላይ የመናገር እና ሀሳብ የመስጠት መብቱን ገድቦ ፍፁም አፈና እየፈፀመ ያለው ወያኔ ዛሬ ደግሞ የህዝብ ጥያቄዎች በስብሰባ አዳራሽ ውስጥ ለምን ይነሳል በሚል ፍርሀት እጅግ ወደር የሌለው ጭልጥ ያለ አምባገነናዊ አፈና መፈፀሙ የሚያሳዝንና የሚያሳፍር ነው ሲሉም የግል ጋዜጣ አዘጋጆች በምሬት ገልጸዋል፡፡

በቅርቡ ሀበሻ ሪቪው የተሰኘ የግል ጋዜጣ አሳታሚ ድርጅት ፍቃድ ተሰጥቶት ወደ ስራ ሊገባ በተዘጋጀበት ወቅት ድንገት ከጀርባችሁ ማን እንዳለ ማጥናት ያስፈልገናል በማለት የወያኔው ተላላኪ ሽመልስ ከማል ፍቃዱን የከለከላቸው ከመሆኑም ባሻገር የዜግነት መብታቸውን ጭምር የገፈፈ ተግባር መፈጸሙን ለጉዳዩ ቅርበት ያላቸው ወገኖች ሲገልፁ ተደምጠዋል፡፡

በሌላ ዜና በመቀሌ ከተማ ዙሪያ የሚገኙ የእንደርታ ቀበሌ ነዋሪዎች በወያኔ ፈጥኖ ደራሽ እና የፌዴራል ፖሊሶች ድብደባና ወከባ እንደደረሰባቸው ከስፍራው የደረሰን ዘገባ አስታወቀ፡፡

በማዘጋጃ ቤት በኩል ህጋዊ በሆነ መንገድ ቦታ የተሰጣቸውና ቦታው ላይ ቤት ሰርተው መኖር ከጀመሩ ከ10 ዓመታት በላይ ያስቆጠሩ የመቀሌ ነዋሪዎች ቤታቸው ድንገት እንዲፈርስ በከተማዋ ካድሬዎች ውሳኔ በመሰጠቱ አቤቱታ ለማቅረብ በተዘጋጁት ዜጎች ላይ ቅልብ የክልሉ ፈጥኖ ደራሽ ፖሊሶች እና በፌዴራል ፖሊስ ከፍተኛ ድብደባ ከመፈጸሙም በላይ ቁጥራቸው የበዙ ነዋሪዎች ተፍሰው ለእስር እንደተዳረጉ ከስፍራው የደረሰን ዘገባ አስረድቶዋል፡፡

የደረሰባቸውን ግፍ እና በደል ለመግለፅ ሰላማዊ ሰልፍ እንዳያደርጉ የተከለከሉት እነዚሁ አቤቱታ አቅራቢ የመቀሌ ነዋሪዎች አቤቱታ ለማቅረብ ቀርቶ በህብረት አንድ ላይ ቆመው በመነጋገር ላይ እንዳሉ ከየት መጡ ሳይባል የፌዴራል ፖሊሶች በአስለቃሽ ጭስ እየተጠቀሙ ከየሰፈሩ እያባረሩዋቸው መሆኑን ያጋለጠው የደረሰን ዘገባ ከዚህ አልፎ ተርፎ የከፋ ድብደባና ርግጫ እንደደረሰባቸው ዘገባው ጨምሮ ገልፆዋል፡፡

የከተማዋ ካድሬዎች እራሳቸው በህጋዊ መንገድ መርተው የሰጡዋቸው መሬት ላይ ቤት ሰርተው እስኪጨርሱ ድረስ ጠብቀው አሁን ግንባታው ህገ ወጥ ነው ማለታቸው በህዝብ ላይ እየተጫወቱና እየቀለዱ መሆኑን ያሳያል ሲል የደረሰን ዘገባ አስረድቶዋል፡፡

ከኤርትራ ለመጡ ተፈናቃዮች ጭምር መሬት ሲያድል የቆየው የመቀሌ አስተዳደር ቤት ሰርተው ኑሮ ከጀመሩ 10 ዓመታት በላይ ባስቆጠሩት ኢትዮጵያውያን ላይ ድንገት ምክንያቱ ምን እንደሆነ ሳይታወቅ ላፈርሰው ነው ማለቱ እጅግ ግራ የሚያጋባ ጉዳይ ነው ሲሉም የችግሩ ሰለባዎች እያለቀሱ ሲናገሩ ተደምጠዋል ሲል ዘገባው አትቶዋል፡፡

ከ10 ዓመት በላይ ከኖሩበት ሰፈር እንዲለቁ እየተገደዱ ያሉት ነዋሪዎች ያወጣነው ወጪ ተሰልቶ ህጋዊ ክፍያ ተደርጎልን እንድንነሳ ብንጠይቅም የሚሰማን ያጣን በመሆኑ መላው የኢትዮጵያ ህዝብ የደረሰብንን በደል እና ግፍ አውቆ የበኩሉን ድጋፍ እንዲያደርግልን ሲሉ መማጸናቸውንም ዘገባው አስረድቶዋል፡፡

ዛሬ ወያኔ ዘር..... ቀለም..... ብሔር..... ሐይማኖት ሳይል በጅምላ ወደር የለሽ ግፍ እየፈጸመ ባለበት ሰዓት መልሶ ለአባይ ግድብ እጃችሁን ዘርጉ ማለቱ እያነቡ እስክስታ ነው የሆነብን ሲሉም እነዚሁ የችግሩ ሰለባዎች ሲናገሩ እንደተደመጡ ዘገባው አጋልጦዋል።

የሚያሳዝነው እና የሚያሳፍረው ይላሉ የመቀሌ ተፈናቃይ ነዋሪዎች የሚያሳዝነው ባለስልጣናቱ የሚታረስ መሬት አይሸጥም አይለወጥም በማለት ከኖርንበት ቤታችን በፖሊስ እየበደቡ ቢያስወጡንም ዛሬ በመላ ሀገሪቱ ውስጥ በሺህዎች የሚቆጠሩ የገበሬ ማሳዎችን እየነጠቁ ለውጭ ሀገር ዜጎች እያከፋፈሉ ያውም የሀገር ሀብት የሆነውን ደን እያስጨፈጨፉ እያየንና እየሰማን ለእኛ እንዲህ ያለ ምላሽ መስጠታቸው እውን እኛ ማን ነን ብለን እራሳችንን ለመጠየቅ እንገደዳለን ብለዋል ሲል ዘገባው አስረድቶዋል።

በተለይ የክልሉ የወያኔ ባለስልጣናት ህገ ወጥ ነው ያሉዋቸውን ቤቶች ለማፍረስ መወሰኑን በመቃወም ሚያዚያ 14 ቀን 2003 ዓ.ም በብዙ ሺህዎች የሚቆጠሩ ዜጎች አቤቱታ ለማቅረብ ወደ ክልሉ አስተዳደር ጽህፈት ቤት በማምራት ላይ እንዳሉ በአውላላ መንገድ ላይ በፌዴራል ፖሊስ አስከብበው ከማስደብደባቸውም በላይ አስተባባሪ ናቸው የተባሉትን ከ50 በላይ የሚሆኑትን ጠልፈው የት እንዳደረሱዋቸው ያልታወቀ መሆኑንም ከስፍራው ደረሰን ዘገባ አጋልጦዋል።

ይፈርሳል ተብሎ በወያኔ ባለስልጣናት የተወሰነበት ሰፈር ውስጥ አርሴማ ማርያም የተሰኘች ቤተክርስቲያን የምትገኝ በመሆኑ እሱም ይፈርሳል በመባሉ የተደናገጡት የአካባቢው ህዝብ ታቦቱን ተሸክሞ ባለስልጣቱን ለመማጸን በአደባባይ ላይ ቢወጣም የጠበቃቸው ዱላ መሆኑን ያጋለጠው የደረሰን ዘገባ እብሪት የወጠራቸው እነዚሁ ባለስልጣናት ታቦት የተሸከሙትን የእምነት አባቶች ጭምር በቆመጥ ሲቀጠቅጡዋቸው እንደነበርም ዘገባው አጋልጠዋል።

አቤቱታ አስተባባሪ ናቸው ተብለው ታፍሰው የታሰሩት ከ50 በላይ አባ ወራዎች ይህ ዘገባ እስከተጠናቀረበት ግዜ ድረስ የት እንደታሰሩ የማይታወቅ መሆኑን ቤተሰቦቻቸው እየገለፁ እንደሚገኝም ተገልፆዋል።

ዛሬ በመላ ሀገሪቱ ውስጥ የተንሰራፋው የወያኔ ባለስልጣናት ሙስና ተግባር በትግራይ ክልል ውስጥም በተመሳሳይ ተንሰራፍቶ ዜጎች በግልጽ ጉቦ ካልሰጡ ምንም አይነት ጉዳይ እንደማይፈጸምላቸው በይፋ በአደባባይ እየተናገሩ መሆኑንም የደረሰን ዘገባ አብራርቶዋል።